*በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም*

# የወባ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ - ኪጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

**ነሐሴ 2001 □/ም**

**አዲስ አበባ**

*በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም*

# የወባ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ - ኬጅ

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**

**ነሐሴ 2001 □/ም**

**አዲስ አበባ**

# ማውጫ


1. መግቢያ---------------------------------------------------------- 1
2. ዓላማ ---------------------------------------------------------- 4
    2.1. አጠቃላይ ዓላማ --------------------------------------- 4
    2.2. ዝርዝር ዓላማዎች-------------------------------------- 4
3. የማስፈፀሚያ ስልት ------------------------------------------------ 5
4. የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት ---------------------------------- 6
5 የወባ በሽታ የመከላከያና መቆጣጠሪያ ስልቶች--------------- 7
    5.1 የመረጃ አሰባሰብ --------------------------------------- 8
    5.2 የጤና አጠባበቅ ትምህርት ---------------------------- 9
6 የወባ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዘዴዎች----------------- 13
    6.1 የአካባቢ ቁጥጥር ---------------------------------------- 13
    6..2 የፀረ እጭ ኬሚካል ርጭት ------------------------- 18
    6.3 በፀረ ትንኝ ኬሚካል በተነከረ አጐበር መጠቀም 22
    6.4 የወባ በሽታ ምርመራና ሕክምና -------------------- 25
7. የወባ ወረርሽኝ መከላከልና መቆጣጠር------------------------ 31
8. የወባ በሽታ ለመከላልና ለመቆጣጠር □□ራ.. ----------------- 40
9. ሰርቶ ማሳያ በመጠቀም ---------------------------------------- 44
10. የሚጠበቁ ውጤቶች --------------------------------------------- 46
11. የመልእክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች ---------------------------- 47
12. ክትትልና ግምገማ ---------------------------------------------- 50
13. ዕዝል 1 የተከናወኑ ተግባራት ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ---- 53

# 1.መግቢያ

በአገራችን ወባ በቆላማ አካባቢዎችና ከፍታቸው ከ2000 ሜትር በታች በሆኑ የወይና ደጋ አካባቢዎች ሁሉ ይተላለፋል። በአንዳንድ ወቅት ከዚህ ከፍታ በላይም ቢሆን ለትንኞች መራቢያ ተስማሚ ውሃ፣ ሙቀትና በቂ የአየር እርጥበት በሚፈጠርበት ጊዜና ቦታ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ ጉዳቱ ግን ከፍተኛ የሆነ ወረርሽኝ ሊከሰት ይችላል። ይኸው ክስተት አልፎ አልፎ እስከ 2500 ሜትር ከፍታ በአገራችን እንደደረሰ መረጃዎች ያመለክ□ሉ። በሽታው በአብዛኛው ከክረምት ወራት በኋላ ከመስከረም እስከ ታህሣሥ በከፍተኛ ደረጃ የሚተላለፍ ሲሆን በአንዳንድ ቦታዎች ከበልግ ዝናብ በኋላ ከሚያዝያ እስከ ግንቦት በመጠነኛ ደረጃ ይተላለፋል።

ከሃገራችን የመሬቱ የቆዳ ስፋት 75 በመቶ ለወባ በሽታ መተላለፍ አመቺ ሲሆን ከአጠቃላይ የአገሪቱ ሕዝብ 68 በመቶ ለበሽታው የተጋለጠ መሆኑ ይገመታል። የወባ በሽታ መተላለፍ

በአየር ሁኔታና በመሬት አቀማመጥ ምክንያት ተለዋዋጭ በመሆኑ በየጊዜው በወረርሽኝ መልክ እየተነሳ በሕብረተሰቡ ሕይወት ላይ ከፍተኛ የሆነ ህመምና ሞት ያስከትላል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሩ ምርቱን እንዳይሰበስብ ወይም ማሳውን እንዳያርስ፣ ተማሪ□ ትምህርቱን እንዳይከታተል ሰራተኛው ስራውን በአግባቡ እንዳይወጣ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ይህም ማለት በሽታው ከሚያስከትለው ሞትና ሕመም በተጨማሪ በእያንዳንዱ ቤተሰብ ገቢና በአጠቃላይም በሃገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያስከትላል ማለት ነው፡፡

እ.አ.አ በ1958 በሃገራችን ተከስቶ በነበረው ከፍተኛ የወባ ወረርሽኝ 3 ሚሊዮን ሰዎች በበሽታው እንደተጠቁና ከነዚህ ውስጥ 150 ሺህ ሰዎች መሞታቸው ይታወቃል፡፡ ከዚያም በኋላ ቢሆን እ.አ.አ. በ1965/66፣ 1972/73፣ 1980/81፣ 1987/88 1992 እና 2003 በሽታው በሃገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች በመከሰት ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል፡፡

በወባ በሽታ ቁጥጥር ዙሪያ □ሁሉም ህብረተሰብ ክፍሎችና አጋር ድርጅቶች ተሳትፎ የጎላ ለማድረግ በአገራችን "ሮል ባክ ማላርያ"በተባለ አቅጣጫ ኘሮ□ራም ተቀይሶ የሕብረተሰቡንና የሌሎች ድርጅቶችን ተሳትፎ የሚያካትት ሕዝቡ በራሱ የበሽታውን ምንነትና የመተላለፊያ መንገዶችን በመገንዘብ ሊወስዳቸው የሚገባቸውን የመከላከያ እርምጃዎች እንዲወስድ የማስተማርና የማብቃት ተግባራዊ ሥራ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ □ህ የወባ መከላከያና መቆጣጠሪያ ኤክስቴንሽን ፖኬጅ እነዚህን አንደምታዎች በማገናዘብ ተዘጋጅቷል፡፡

# 2. ዓላማ

## 2.1. አጠቃላይ ዓላማ

- በወባ በሽታ ሊደርስ የሚችል ሕመም ለመቀነስና በዚሁ ሳቢያ የሚደርሰውን ሞት በከፍተኛ □ረጃ በመቀነስ ብሎም በማስቀረት የሕብረተሰቡን ጤና መጠበቅ፣

## 2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- ሕብረተሰቡ ስለወባ በሽታ መተላለፊያና መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ላይ ያለውን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ በመከላከል ሥራ ላይ እንዲሳተፍ ማስቻል፣
- ሕብረተሰቡን በወባ ቁጥጥር ሥራ ላይ በማሳተፍ ሊከሰት የሚችለውን የወባ ወረርሽኝ ለመቀነስ ከተከሰተም ብዙ ጉዳት ሳይደርስ መቆጣጠር፣
- በወባ በሽታ የተያዘ ሰው ለከፍተኛ ጉዳት ሳይደርስ ወደ ሕክምና የመሄዱን ጥቅም ለህብረተሰቡ በማሳወቅ በሕክምና የመጠቀም ልምድን ማሳደግ፣

## 3 የማስፈጸሚያ ስልት

3.1. የወባ በሽታ መነሻ ጥናት (ቅኝት) በማካሄድ፣

3.2. ሕብረተሰቡ ስለወባ በሽታ መተላለፊያና መቆጣጠሪያ መንገዶችን ተረድቶ ለተግባራዊነቱ ተሳትፎ እንዲያደርግ ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው ትምህርት በመስጠት፣

3.3. በወባ መከላከልና መቆጣጠር ሥራ የቤተሰብ ተሳትፎ ማጎልበት፣

3.4. የተመረጡና ቀጣይነት ያላቸው የቬክተር ቁጥጥር ስራዎች በማካሄድ፣

3.5. የወባ ወረርሽኝ ሳይከሰት አስቀድሞ መከላከልና ከተከሰተም ጉዳት ሳያደርስ መቆጣጠር፣

3.6. በቀበሌው ውስጥ ከሚሠሩ ማንኛውም ሕዝባዊ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ቅንጅታዊ አሠራር በመፍጠር በጋራ መሥራት፣

# 4. የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

4.1. ለወባ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ መረጃዎች መሰብሰብ፣

4.2. ስለወባ በሽታ ምንነት፣ የመተላለፊያ መንገዶች፣ ስለሚያስከትለው ጉዳትና የመከላከያ ዘዴዎች ሕብረተሰቡን ተከታታይነት ባለው መንገድ ማስተማር፣

4.3. የወባ ትንኝ መቆጣጠሪያ ዘዴ

- የወባ ትንኝ መራቢያ ቦታዎችን ለይቶ በማወቅ ሕብረተሰቡን አስተባብሮ በአካባቢ ቁጥጥር ሥራ ላይ ማሳተፍ፣
- ቋሚና በአካባቢ ቁጥጥር ሥራ ሊወገዱ የማይችሉትን የወባ ትንኝ መራቢያ ቦታዎች ለይቶ በማወቅ የፀረ-እጭ ኬሚካል በመርጨት መቆጣጠር፣
- የወባ ትንኝ መከላከያ ዛንዚራ (አጎበር) አጠቃቀም በቤተሰብ ዘንድ እንዲለመድ ማድረግ፣

4.4. ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ በምትሠራበት ወባማ አከባቢ በወረርሽኝ ጠቋሚ ቻርት በመከታተል የወባ ወረርሽኝን በወቅቱ መቆጣጠር፣ ወረርሽኙ ከአቅም በላይ ሲሆን ለእገዛና ድጋፍ ለሚመለከተው ጤና ጽ/ቤት ሪፖርት በማድረግ ወረርሽኙ ጉዳት ሳያስከትል በቁጥጥር ሥር እንዲውል ማድረግ፣

4.5. የቤተሰቡ አባላት በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የግልና የጋራ ድርሻቸውን እንዲወጡ ማስተባበርና መቀስቀስ፣

## 5. የወባ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ ስልቶች፣

የወባ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተነደፉት ስልቶች በአብዛኛው የወባ አስተላላፊ ትንኞችን እንዳይራቡ በማድረግ፣ ከተራቡ ደግሞ በማጥፋት ወይንም በሰውና በትንኝ መካከል ያለውን ግንኙነት በማቋረጥ የሚካሄዱ ሲሆኑ የበሽታውን የመተላለፊያ ሂደት ለመግታትም

ያስችላል፡፡ በመሆኑም የተለያዩ የወባ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ዘዴዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

## 5.1. የመረጃ አሰባሰብ

በቀበሌው የሚገኙትን መሠረታዊ መረጃዎች መሰብሰብ፡፡

- ❖ የቀበሌ ሕዝብ ብዛት በፆታና ዕድሜ፣
- ❖ በቀበሌ ውስጥ ያሉ የውሃ አካላት ስፋትና ብዛት፣
- ❖ በቀበሌው የሚገኙ የግልና የመንግሥት የሕክምና መስጫ ተቋማት፣ ት/ቤቶች፣ ሕዝባዊ ማህበራት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣
- ❖ የወባ በሽታ የቀበሌው የጤና ችግር መሆኑን መለየት፣
- ❖ □የተወሰዱ ያሉ የወባ ቁጥጥር ሥራዎች
- ❖ የህብረተሰቡ ለወባ ቁጥጥር ያለዉ አቅም (□እዉቀት፣ □□□፣ የገንዘብ፣ □ቁሳቁስ የአደረጃጀትና የአመለከከት ሁኔ□)

## 5.2. የጤና አጠባበቅ ትምህርት

### 5.2.1. የወባ በሽታ ምንድን ነው?

የወባ በሽታ ኘላስሞድየም በተባሉ ረቂቅ ጥገኛ (ፖራሳይትስ) ተህዋስያን የሚመጣ በሽታ ነው:: በሰው አካል ውስጥ በመራባትና በማደግ ለበሽታው የሚያጋልጡ አራት የኘላስሞድየም ተህዋስያን ዝርያዎች ብቻ ናቸው:: እነሱም:-

- ኘላስሞዲየም ፋልሲፖረም
- ኘላስሞዲየም ቫይቫክስ
- ኘላስሞዲየም ማላሪዬ
- ኘላስሞዲየም አቫሌ ይባላሉ::

ተህዋስያኑ የተለያየ የቅርፅ፣ የእድገት፣ የትውልድ ብዛት፣ ለመራባት የሚወሰዱት የጊዜ ፍጆታ፣ የበሽታው ጥንካሬ፣ በሰው ላይ የሚያሳዩት የግርሻ አይነትና ወቅት በመድኃኒቶች የመጠቃት ዝንባሌ፣ በአካል ውስጥ የሚያደርሱት ጉዳት ዓይነት የተለያየ ነው:: ከነዚሁ የወባ ተህዋስያን ዝርያዎች በሃገራችን ደረጃ በዋነኛነት የሚገኙት

ኘላስሞዲየም ፋልሲፖረምና ኘላስሞዲየም ቫይቫክስ ናቸው::

የወባ በሽታ በጤና ላይ የሚያስከትለው ጉዳት የደም ህዋሳትን በመጨረስ፣ የአእምሮ መዳከም፣ እንደጉበት ኩላሊት አንጎል በሚገኙ የውስጥ አካላት ላይ ቀውስ በመፍጠር፣ ጉስቁልና ችግርና ሞት ያስከትላል:: በነፍሰጡሮች፣ በወላጆችና በሕፃናት ላይ ከባድ ጉዳትና ሞት ከማድረሱም ባሻገር ለሌሎች ተላላፊ በሽታም ያጋልጣል::

### 5.2.2. የወባ በሽታ ስሜቶችና ምልክቶች

የተህዋስያኑ በቀይ ደም ህዋሳት ውስጥ የሚያካሂዱትን የማደግና የመራባት ሂደት በመጨረስ ከቀይ ደም ህዋሳት ውስጥ በመውጣትና በመሰራጨት እንዲሁም ወዲያውኑ ቀጥለው ሌሎች ጤነኛ የደም ህዋሳትን ከማጥቃት ሁኔታ ጋር የስሜቶችና የምልክቶች መከሰት የተያያዘ ነው::

- በሽተኛው ህመም ሲጀምረው የብርድ ብርድ ማለት ስሜት ይከሰታል፣

- ትኩሳትና ማላብ፣
- ምግብ ማስጠላት ቢመገብም ማስመለስ፣
- ራስ ምታትና ውሃ ጥማት፣
- በጀርባና በአካል መገጣጠሚያዎች ቁርጥማት መሰማት::

### 5.2.3. የወባ በሽታ መተላለፊያ መንገድ

የወባ በሽታ ከአንድ ሰው ወደ ሌላው የሚተላለፈው በሴቷ አኖፌለስ በምትባል የወባ ትንኝ ዝርያ ንክሻ አማካኝነት ብቻ ነው::


ትንኝ ሁሉ ወባን አያስተላልፍም:: የወባ አስተላላፊ ትንኝዋ የምትጥለው እንቁላል እንዲዳብር የሚያስፈልጋት ምግብ ደም ነው:: ከአንድ በወባ የታመመ ሰው በአጋጣሚ ደም ስትመጥ፣ የወባ በሽታ ተህዋስያን ከደሙ ጋር በመውሰድ በሆዷ ውስጥ ከ10-12 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በማደግና ቅርፃቸውን በመለዋወጥ ይራባሉ::

ከዚያም በኋላ ይህች ትንኝ እንደገና ደም ለመመገብ ጤነኛን ሰው ስትነክስ የምትመጠው ደም እንዳይጓጉል /እንዳይረጋ/ በመጀመርያ ምራቋን በምትረጭበት ጊዜ ጥገኛ ተህዋስያኑም ከምራቅ ዕጢ ውስጥ ከምራቅ ጋር ተቀላቅለው ወደ ጤነኛው ሰው ደም ሥር ይገባሉ፡፡

በጤነኛ ሰው ደም ውስጥ ትንኟ ጥገኛ ተህዋስያኑን ስትተፋ ወዲያውኑ ህመም አይሰማም፡፡ ስሜት ሳይሰማው ግለሰቡ የተለመደ የዕለት ተዕለት ተግባሩን እያከናወነ ከ10-14 ቀናት ደህና ሆኖ ይሰነብታል፡፡ በነዚህ ቀናት ውስጥ በጉበቱ ውስጥ ተህዋስያኑ ገብተው ይራባሉ፡፡ ከጉበት ህዋሳት እድገታቸውን ጨርሰው ወደ ደም ቧንቧ በመሠራጨት ቀይ የደም ህዋሳትን ይወራሉ፡፡ ይህም ክስተት በአራቱም የወባ ዝርያዎች የተለያየ ጊዜና ጠባይ አለው፡፡

የወባ አስተላላፊ ትንኝ የምትራባው በአብዛኛው ከዝናብ ወራት በኋላ በየአካባቢው ተጠራቅሞ

በሚቆይ ውሃ ውስጥ ነው:: እንቁላሎቹ በውሃው ላይ ወደ እጭና ኩብኩባ ከተለወጡ በኋላ እድገታቸውን ሲጨርሱ ትንኞች በመሆን ከውሃው ላይ በረው ይሄዳሉ:: የወባ ትንኝ ከመራቢያ ቦታዎች እስከ 2 ኪ.ሜ በመብረር ሰውን መንደፍ ትችላለች:: የወባ ትንኝ ደም ለመመገብ የምትንቀሳቀሰዉ በምሽትና በሌሊት ብቻ ነው::




ስዕል 1 የትንኝ አረባብ ሂደት

# 6. የወባ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዘዴዎች

## 6.1 የአካባቢ ቁጥጥር

የወባ አስተላላፊ ትንኞች ለመራባት የግድ ውኃ ያስፈልጋቸዋል:: ስለዚህ በሰዎች መኖሪያ

አቅራቢያ የሚገኙትንና በጊዜያዊነት የሚፈጠሩትንም ሆነ በቋሚነት የሚኖሩትን አገልግሎት የማይሰጡ ውኃ ያቆሩ ሥፍራዎችን ሕዝቡን አስተባብሮ በማስ□□□ ለትንኝ መራባት አመቺ እንዳይሆኑ በማድረግ የወባ በሽታን መከላከልና መቆጣጠር ይቻላል።

ሆኖም ይህ የቁጥጥር ሥልት ውጤታማ የሚሆነው ትንኞች ሙሉ በሙሉ እንዳይራቡ ማድረግ ወይንም ቁጥራቸውን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ሲቻል ብቻ ነው። ይህንን ውጤት ለማምጣት የሚቻለው ደግሞ የትንኝ መራቢያ ሥፍራዎች በቁጥር ውስን ሆነው ሙሉ በሙሉ ለመለየትና ለመቆጣጠር የሚቻልባቸው ቦታዎች ነው። እነዚህም በአብዛኛው በረሃ ቀመስ ቦታዎች፣ ወባማ ከተሞች፣ የልማት ተቋሞችና በሌሎችም ቦታዎች በደረቅ-ወራት ናቸው። የትንኝ መራቢያዎች በስፋት በተሰራጩበት ቆላማና ወይና ደጋማ የገጠር አካባቢ የመራቢያ ቦታዎች ለመለየትና ለመቆጣጠር አዳጋች በሚሆንበት የክረምት ወቅት ይህን ተግባር

ማቀጹ ጥቅም የሌለውና ሀብት (የሰው ጉልበት ፣ ጊዜና ገንዘብ) ማባከን ሊሆን ይችላል፡፡

በአገራችን በዋነኛነት የወባ በሽታን የምታስተላልፈው ትንኝ ለመራባት የምትመርጠው የተከማቸ ንፁህ ውኃ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተቆራረጠ ወንዝ ላይ፣ በኩሬዎች ዳርቻ፣ በረግረጋማና ጨፌ ቦታዎች፣ በዝግታ በሚንቀሳቀስ የመስኖ ውኃ፣ እንዲሁም ጥልቀት በሌለው የግድብ ዳርቻ ልትራባ ትችላለች፡፡ ስለዚህ በመራቢያ ቦታዎች ላይ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እርምጃዎች በመውሰድ የወባን በሽታ መቆጣጠር ይቻላል፡፡

- የትንኞች መፈልፈያ የሆኑና አገልግሎት የማይሰጡ ሰውሰራሽና የተፈጥሮ ጉድጓዶችን መሙላት፣ መደልደልና ማስተካከል፣
- ረግረግ ቦታዎችን ቦይ በመቅደድ ውኃውን ማፋሰስ ወይም ውሃ በብዛት የሚመጡ እንደ ባህር ዛፍ የመሳሰሉ ዛፎችን በመትከል እንዲደርቅ ማድረግ፣

- በደረቅ ወራት የተቆራረጡና ኩሬ የፈጠሩ ወንዞችን በመጥረግ በፍጥነት እንዲፈሱ ማድረግ፣
- የመስኖ አርጅኖችን በመጥረግና ውስጣቸው የበቀለ ሳርና አረም በማጨድ/በመንቀል በፍጥነት እንዲፈሱና ውኃ ከአርጅኖቹ ውጭ እንዳይጠራቀም መንከባከብ፣ በሳምንት አንድ ቀን የመስኖ ውኃ በኃይል በመልቀቅ የተጣሉ የትንኝ እንቁላሎች ካሉ ጠራርጐ እንዲወስድ ማድረግ ወይም በሳምንት ለአንድ ወይም ለሁለት ቀናት የመስኖውን ውኃ በመዝጋት ሙሉ በሙሉ እንዲደርቅ አድርጐ ከዚያም በማግስቱ ውኃውን በኃይል መልቀቅ፣
- በቤት ውስጥና ውጭ የሚገኙ የውኃ ማስቀመጫ እንሥራዎች፣ በርሜሎች፣ ቢርካና ጉድጓዶች መክደን፣
- አገልግሎት የማይሰጡ በቤቶች ዙሪያ የተጣሉ የተለያዩ ውኃ አቁረው የሚይዙ ቁሳቁሶች እንደ እንሥራ ስባሪዎች፣ አሮ◻ ጐማዎች፣ ወዘተ... ማስወገድ፡፡

የአካባቢ ቁጥጥር ለማከናወን የሚረዱ ሁኔታዎች ቅደም ተከተል፡-

1. የትንኝ መራቢያ ቦታዎች ስፋትና ብዛት ለይቶ ማወቅ፣
2. የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛት ማወቅ፣
3. ለሥራው የሚያስፈልገው የመሣሪያ አይነትና ብዛት መለየት፣
   - አካፋ
   - ዶማ
   - ማጭድ
   - ቆንጨራ
   - ባሬላ ወይም ጋሪ ወይም ጆንያ
4. የአካባቢ ቁጥጥር ሥራ የሚፈጀው ጊዜ መገመት፣
5. በአካባቢ ቁጥጥር □□ የሚወስደው እርምጃ /ማዳፈን፣ ማፋሰስ፣ ቦይ መቅደድ፣ በውሃ መውረጃ ቦይ የሚበቅለውን እፀዋት ማጨድ/መወሰን፣
6. በተወሰነው ቀንና ቦታ ሥራውን መምራት፣
7. የተሠራውን ሥራ መዝገቦ መያዝ፣ውጤቱንም መከታተልና መገምገም፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት የአካባቢ ቁጥጥር ሥራዎች ከፍተኛ የሰው ጉልበት የሚጠይቁ በመሆኑ የሚከናወኑት በሕብረተሰቡ ተሳትፎ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሥራዎቹም በቀጣይነት እንደአስፈላጊነታቸው በየሣምንቱ መካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡ የትንኝ መራቢያ ሥፍራዎችን በመለየት መወሰድ ያለበትን እርምጃ በተመለከተ የጤና የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ህብረተሰቡን በመቀስቀስና በማሳመን ከሚያበረክቱት ትምህርት ውጭ የቴክኒክ እገዛም ያደርጋሉ፡፡

### 6.2 የፀረ እጭ ኬሚካል ርጭት

በማዳፈን ወይም በማፋሰስ ለማስወገድ የማይቻሉ □ቋቱ የውኃ ቦታዎች ላይ የትንኞችን እጭ የሚገድሉ የተለያዩ ኬሚካሎች መርጨት ይቻላል፡፡ እንደ አካባቢ ቁጥጥር ሁሉ የዚህ ስልት ውጤታማነት የሚወሰነው በአካባቢ የሚገኙ የትንኝ መራቢያዎችን ሙሉ በሙሉ በመለየት አስፈላጊውን ርጭት በየሳምንቱ በቋሚነት በማካሄድ ነው፡ ይህ ሥራ በአብዛኛው

ከአካባቢ ቁጥጥር ሥራዎች ጋር በጥምር መካሄድ አለበት::

በአገራችን የትንኝ እጮች ለመግደል በውሃ አካላት የሚረጨው ኬሚካል "ቴሞፎስ" (አቤት) በመባል ይታወቃል:: ይህ ኬሚካል ለመጠጥ በሚያገለግሉ የውኃ ክምችቶች ላይ ጭምር ሊረጭ ይችላል::

ስለዚህ ከኬሚካል ፍጆታ፣ ከመሣሪያ አቅርቦትና የሰው ኃይል ፍላጐት አንጻር ይህ የቁጥጥር ዘዴ ተመራጭ የሚሆነው የትንኝ መራቢያ ሥፍራዎች አነስተኛ በሆኑበትና ሌሎች እርምጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በማይቻልባቸው እንደ ትላልቅ ከተሞች፣ በረሃማ አካባቢዎች፣ የመስኖ ልማት በሚካሄድባቸው እርሻዎች ውስጥ ነው::

እቤት ኬሚካል ርጭት ቅደም ተከተል


1. ለሰውና ለእንስሳት አገልግሎት የሚውልና የአኖፌለስ ዕጭ ያለበት የመራቢያ ቦታ ስፋት በካሬ ሜትር ማወቅ፣
2. ለ40 ካሬ ሜትር አንድ ሲሲ አቤት ኬሚካል በአንድ ሊትር ውሃ ስሌት ማዘጋጀት፣
3. በኬሚካል መርጫ መሳሪያው ውስጥ ኬሚካሉንና ውሃ ማዋሃድ፣
4. የሚፈለገውን የአየር ግፊት (60 ጊዜ መንፋት) መስጠት፣
5. ልምድ ባለው ሰው በመጠቀም መርጨት፣
6. የተሠራውን ሥራ መዝግቦ መያዝ፣ ስለ ር□ ቱ፣ ዉጤትም መከታተልና መገምገም::

እቤት ኬሚካል የማይረጭበት ሁኔታ:-

ለቤት ኬሚካል በሚረጭበት ጊዜ ዝናብ የሚጥል ከሆነ ኬሚካሉን ጎርፍ ስለሚያጥበው (ስለሚወስደው) ከመርጨት መቆጠብ ያስፈልጋል::

## ማሳሰቢያ

**የወባ አስተላላፊ የአኖፌለስ ትንኝ ዕጭ ከሌሎች ትንኞች ዕጭ ጋር ሲነፃፀር ከውሃው ገፅ ላይ ትይዩ ሆኖ በመንሳፈፉ ነው::**




*ሥዕል 2. አኖፌለስ ትንኝ ከሌሎች ትንኞች የምትለይበት መንገድ*

## 6.3 በፀረ ትንኝ ኬሚካል በተነከረ አጐበር መጠቀም:-

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ አገሮች የወባ በሽታ ህመምና ሞት በመቀነስ ረገድ ውጤት ካሳዩት ዘዴዎች መሃል በግንባር ቀደም የሚጠቀሰው በኬሚካል የተነከሩ አጐበሮች መጠቀም ነው:: ይህ ዘዴ ትንኞችን በመግደልና በአጐበሮች ላይ እንዳያርፉ በማባረር ከትንኝ ንክሻ ለመከላከል ያስችላል:: በአገራችን ይህ አሰራር ያልተለመደ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህብረተሰቡ እንዲለመድ ጥረት እየተደረገ ነው:: አጐበሮች በተለያየ (መጠን፣ ቅርፅ፣ ቀለም እንዲሁም የተሰሩበት ጨርቅ) ዓይነት ይገኛሉ::

### የአጎበር ቅርጽ

በአብዛኛው የምንጠቀምባቸው አጐበሮች ባለ አራት ማዕዘንና ክብ ቅርፅ ያላቸው ሲሆኑ በአገራችን በስፋት ተሰራጭቶ የሚገኘው ግን ባለአራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ነው:: ይህ ተመራጭ የሆነበት ዋና ምክንያት:-

- አጐበሩ በአራት ማዕዘን ስለሚወጠር የሰውነት ክፍሎች ከአጐበሩ ጋር የመነካካት እድል ስለማይኖር፣
- ከቤት ውጪ ለሚተኙ ሰዎች ዘርግቶ ለመጠቀም ቀላል በመሆኑ፣
- ባለ አራት ማዕዘኑ ከክቡ አጐበር ጋር ሲነፃፀር ዋጋው ርካሽ ስለሆነ ነው::

## የአጎበር መጠን

በገበያ ላይ የተለያየ መጠን ያላቸው የአጐበር ዓይነቶች ይገኛሉ:: እነሱም:-

ሠንጠረዥ 1 በገበያ ላይ የሚገኙ የአጐበር ዓይነቶች

| የአጐበር ስም | ስፋት (በሳ.ሜትር) | ቁመት (በሳ.ሜትር) | ከፍታ (በሳ.ሜትር) |
|---|---|---|---|
| ለአንድ ሰው | 70 | 180 | 150 |
| ለሁለት ሰው | 100 | 180 | 150 |
| ለቤተሰብ | 130 | 180 | 170 |
| ለትልቅ ቤተሰብ | 190 | 180 | 170 |

አጐበሮች በቂ ስፋት ኖሮአቸው አልጋውን ወይም ምንጣፉን መሸፈን መቻል አለባቸው:: ስፋታቸው አነስተኛ ከሆነ ከአጐበሩ ጋር የሚፈጠረው ንኪኪ ለትንኝ ንክሻ ያጋልጣል::

የአጐበር ስፋት በጣም ትልቅ ከሆነ ደግሞ ከመኝታው አልጋ ወይም ምንጣፍ ስፋት በላይ ስለሚሆን ለአጠቃቀም አያመችም::

## የአጎበር ቀለም

የአጐበር ቀለም ምርጫ በህብረተሰቡ ባህልና የማጠብ ልምድ ይወሰናል:: በገበያ ላይ አረንጓዴ፣ ሰማያዊና ነጭ ቀለም ያላቸው አጐበሮች ሲኖሩ በአብዛኛው ህብረተሰቡ የሚመርጠው ግን በቀላሉ የማይቆሸሹትን አረንጓዴውንና ሰማያዊውን ነው:: አጎበሩ

የተሰራበት ጨርቅ:-

ገበያ ላይ የሚገኘው አጐበር የተሠራው ከፖሊስተርና ከፖሊ□ትሊን ጨርቅ ነው::

በኬሚካል የተነከረ አጐበር ጥቅም

1. በኬሚካል የተነከረ አጐበር ከትንኝ ንክሻ ይከላከላል፣ የተቀደደም ቢሆን ትንኞችን በሽታ (በጠረን) ያባርራል፣ በአጐበር ላይ ሲያርፉም ይገድላል::

2. የሰውነትንና የትንኝ ንክኪ ይቀንሳል፣
3. የትንኞችንም ብዛት ይቀንሳል፣
4. የትንኞችን በህይወት የመቆየት እድሜ ያሳጥራል፡፡
5. የወባ ትንኞች ብቻ ሳይሆን ሌሎች አዋኪ ነፍሳትንም ይገድላል፡፡
6. በኬሚካል የተነከረ አጐበር በስፋት መጠቀም አጠቃላይ የወባን በሽታ ስርጭት ይቀንሳል፡፡

## 6.4. የወባ በሽታ ምርመራና ሕክምና

### 6.4.1. ምርመራ

የወባ በሽታ ምርመራ የሚመሰረተው ከሕሙማኑ ስሜትና ምልክቶች እንዲሁም ሕመምተኛው ከሚሰጠው አጭር የሕመሙ ታሪክ በመነሳት እንዲሁም ፈጣን የወባ መመርመሪያ (RDT) ወይም ላቦራቶሪ ተሠርቶ በተገኘው የምርመራ ውጤት መሰረት ነው፡፡

ወባማ በሆኑ ቦታዎች

አንድ በሽተኛ ትኩሳት ካለው ወይም ባለፉት 2 ቀናት ውስጥ ትኩሳት እንደነበረው ከገለፀ የወባ በሽታ እንደታመመ ይጠረጠራል፡፡

ወባማ ባልሆኑ አካባቢዎች

በሽተኛው ትኩሳት ካለው ወይም ባለፉት 2 ቀናት ትኩሳት እንደነበረው ከገለፀና በተጨማሪም ባለፉት ሁለት ሣምንታት ጊዜ ውስጥ ወደ ወባማ ቦታዎች ተጉዞ የነበረ ከሆነ የወባ በሽታ እንደታመመ □□ረ□ራል ፡፡

ነገር ግን ሌሎች በጉልህ በአካባቢው የሚታዩ ትኩሳት የሚያመጡ በሽታዎች እንደ ኩፍኝ፣ የሳንባ ምች፣ ማጅራት ገትር የላይኛው የመተንፈሻ አካል በሽታዎች የመሳሰሉት መኖር ያለመኖራቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

## 6.4.2. ህክምና

### የመድኃኒት ሕክምና

የወባ በሽታ ምርመራ ተደርጎለት አስፈላጊውን ህክምና ማግኘት ይኖርበታል፡፡ በዚህም መሰረት ፈጣን መመርመሪያ ዘዴ (RDT) ወይም ላቦራቶሪ ካለ የወባ በሽታ ህክምና ከመሰጠቱ በፊት ከበሽተኛው የደም ናሙና ተወስዶ ምርመራ በማድረግ የወባ ተህዋስያን መኖሩ ይረጋገጣል፡፡ በምርመራው መሰረት የወባ በሽታ መሆኑ ከተረጋገጠ የወባ መድሃኒት □ሰ□ል፡፡

ስለ □ባ የሚከተለውን □ቃሚ መልዕክቶች ይንገሯቸው:-

- ከመድሃኒቱ ጋር በቂ የሆነ በይበልጥ ስብ ያለው ምግብ በመመገብ መድሃኒቱ በቀላሉ እንደሚዋድ፣
- መድሃኒቱን ሳ□ቋር□ּ መውሰድ እንዳለባቸው ማስረዳት፣
- የወባ በሽታ ሕክምና እንደተሰጣቸው፣

- የወባ በሽታ የሚተላለፈው በትንኝ እንደሆነ
- የትንኝ መራቢያ ቦታዎችን በማጥፋትና አጎበር በመጠቀም የወባ በሽታን መከላከል እንደሚቻል፤
- በወቅቱ በመታከም በሽታው ወደ አደገኛ ደረጃ እንዳይደርስ ለማድረግና ሞትን ለማስቀረት እንደሚቻል ማስረዳት ያስፈልጋል
- እርግዝናው 3 ወርና ከዚያ በታች ለሆኑ እናቶች፣ ክብደታቸው ከ5 ኪሎ ግራም በታች ለሆኑ ህፃናት እንዲሁም 3 ወር ያልሞላቸው ህፃናትን ለሚያጠቡ እናቶች ቢሰጥ ጉዳት እንደሚያደርስ ማስረዳት □ስ□ል□ል፡፡

ተጓዳኝ ሕክምና

በወባ በሽታ ሕሙማን ላይ የሚታዩ ሌሎች የጤና ችግሮች፤ ማለትም የሰውነት ፈሳሽ ማነስና (dehydration) ከፍተኛ ትኩሳት ተጨማሪ

ሕክምና ሊያስፈልግ ስለሚችል የሚከተለው □□ረ□፤

- ትኩሳቱን ለማቀዝቀዝ ለብ ባለ ውሃ በተነከረ ስፖንጅ (ጨርቅ) የሰውነቱን ሙቀት ማቀዝቀዝ ወይም ነፋስ እንዲያገኝ ማራገብ፤
- መካከለኛ የሰውነት ፈሳሽ ማነስ (ድርቀት) ላላቸው ሕሙማን ሕይወት አድን ንጥረ ነገር **(ORS)** ይሰዓ፡፡ እንዲሁም ንፁህ ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽ በበቂ ሁኔታ እንዲወስዱ ይምከሩ ፡፡ ከአንድ ወር በታች ለሆኑት ሕፃናት ከተለመደው በላይ እንዲያጠቡ እናቶች □በረታቱ ፡፡

ክትትል

ህመምተኛው የተሰጠውን መድሃኒት በትክክል መውሰዱን ክትትል ያድርጉ፡፡ በሶስት ቀናት ውስጥ ህመሙ ካልተሻለው ወይም ከባሰበት በአፋጣኝ ሪፈራል ወረቀት

ተጽፎለት ወደ ጤና ጣቢያ እንዲሄድ □□ረ□፡፡

ወደ ከፍተኛ ሕክምና መላክ (ሪፈራል) ከሚከተሉት ምልክቶች ውስጥ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ያለው ሕመምተኛ ሲያጋጥምዎት በአፋጣኝ በአካባቢው ወደሚገኘው ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል ይላኩት ፤

- የስሜት ህዋሳት መዳከም ( በትክክል ማሰብ አለመቻል ፣ መፍዘዝ እንዲሁም እራስን መሳት) ፣
- መብላት ወይም መጠጣት  አለመቻል ፣
- በተከታታይ ማስታወክ ፣
- አረፋ እያስደፈቀ ማንቀጥቀጥ ፣
- መቆምና መቀመጥ አለመቻል ፣
- በ24 ሰዓታት ውስጥ ምንም የውሃ ሽንት ያለመኖር ፣
- መድማት (ከድድ ወይም ከሌላ አካል)፣

- የዓይን ቢጫ መሆን ፣
- መተንፈስ ያለመቻልና ፣
- ሌሎች በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ደረጃ ሕክምና ሊደረግላቸው የማይችሉ ምልክቶች ሲኖሩ ፣

ውሃ በተነከረ ስፖንጅ ወይም በማራገብ ትኩሳቱን መቀነስ ፣

በሽተኛው መጠጣት ከቻለ ሕይወት አድን ንጥረ ነገር **(ORS)** ወይም ሌላ ፈሳሽ ይሰዓ፣

በሽተኛው የወሰደውን ነገርና የታዩትን ምልክቶች በሙሉ በሪፈራል ወረቀቱ ላይ □ኑር::

## 7. የወባ ወረርሽኝ መከላከልና መቆጣጠር

የወባ ወረርሽኝ ማለት በአንድ የተወሰነ ቦታና ጊዜ ከተለመደው ቁጥር በላይ የበሽታው ጨምሮ መታየት ነው::

## የወባ ወረርሽኝ መከሰት መንስኤዎች

### 1. የአየር መለዋወጥ

**የዝናብ ሁኔታ**

የዝናቡ መጠን ከሚጠበቀው በላይ ሲሆን በርካታ የወባ ትንኝ የመራቢያ ቦታዎች ይፈጠራሉ፡፡ የዝናቡ መጠን ሲያንስና በደረቅ ወራት ደግሞ ወራጅ ወንዞች እየቀነሱ በሚሄዱበት ጊዜ በሚፈጥሩት አነስተኛ የውሃ ቋጠሮዎች ሳቢያ ለወባ ትንኞች መራቢያ አመቺ ይሆናሉ፡፡

**የአየር ሙቀት/Temprature/**

በደጋና ወይናደጋ አካባቢዎች የአየር ሙቀት መጨመር የወባ ትንኞች የሕይወት ዑደት(Life cycle) ያፋጥናል፡፡ የተህዋስያኑ የህይወት ዑደትም በትንኞች ሆድ ውስጥ በአጭር ቀናት ውስጥ እድገታቸውን እንዲያጠናቅቁ ያደርጋል፡፡

**የአየር እርጥበት፡- /Humidity/**

1. እርጥበት ደግሞ የወባ ትንኞች ረዥም እድሜ እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡
2. የውሃ ልማት ስራዎች መስፋፋት፣ በደንብ ያልተጠበቁ የግድብና የመስኖ ሥራ መስፋፋት ለወባ ወረርሽኝ መከሰት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡
3. የትንኝ ቁጥጥር ሥራዎች መዳከም፣
4. የፀረ ትንኝ ኬሚካል ፍቱንነት መቀነስ፣
5. የትንኞችን የአመጋገብ ባህሪ ከእንስሳት ወደ ሰው መቀየር ፣
6. የሰዎች በብዛት ወባ ከሌለበት ወደ ወባማው አካባቢ ወይም ከወባማው ወደ ወባማ ያልሆነው አካባቢ ሲንቀሳቀሱ
7. የፀረ ወባ መድኃኒቶች ፍቱንነት መቀነስ ናቸው፡፡

## የወባ የወረርሽኝ ክትትል፡-

የወባ ወረርሽኝ ትንበያና አስቀድሞ ማወቂያ ዘዴዎች፣

1. የአየር ጠባይ መረጃ፣
2. የትንኝ ጥናት፣
3. የሕሙማን ሪፖርት ናቸው::

እነዚህ የወረርሽኝ ትንበያና አስቀድሞ ማወቂያ ዘዴዎች ተጨባጭ መረጃ ከመስጠት አንፃር በቅደም ተከተል ከ1 ወደ 3 እየጨመረ ሲሄድ ወቅታዊነታቸው ደግሞ በአንፃሩ እየቀነሰ ይመጣል::

1. የአየር ጠባይ መረጃ

የዝናብ መጠን መጨመረ ወይም በከፍተኛ ደረጃ መቀነሰ የሙቀት መጠን ከሚጠ በቀው በላይ መጨመር እንዲሁም የአየር እርጥበት እስከ 60% ከደረሰ ለወባ በሽታ በወረርሽኝ መልክ መከሰት ምቹ የአየር ንብረት ናቸው:: በመሆኑም ይህ አመቺ ሁኔታ ከተፈጠረ በሣምንታትና ወራት ጊዜ ውስጥ የወባ ወረርሽኝ እንደሚከሰት መተንበይ ይቻላል::

2. የትንኝ ጥናት

የትንኝ ጥናት መረጃዎችን አዘውትሮ መከታተል አስቸጋሪ ቢሆንም በተለይ የትንኝ ዕጮችን ብዛት ለወረርሽኝ በተጋለጡ አካባቢዎች በመከታተል መቆጣጠር ይቻላል፡፡ በአብዛኛውም የአኖፌለስ አረቢያንሲስ ዕጭና የበረሩ ትንኞች ብዛት ከጨመረ የወባ ወረርሽኝ መከሰትን ያመለክታሉ፡፡

3. የሕሙማን ሪፖርት

በየቀኑ ከጤና ተቋማት የሚሰበሰቡ የህሙማን ብዛት ሪፖርት በማሰባሰብና በመተንተን የወባ ወረርሽኝ ሁኔታ መከታተል ይቻላል፡፡ የአምስት አመትና የሕሙማን ሪፖርት በሳምንትና ወራት በመመዝገብና በመተንተን በአካባቢው የተለመደውን /Normal chart/ የወባ ሁኔታ ማወቅ ይቻላል፡፡ ይህም የወረርሽኝ መከታተያ ቻርት /Epidemic Monitoring chart/ በመባል ይታወቃል፡፡

## የወረርሽ መከታተያ ቻርት የአሠራር ቅደም ተከተል

1. የእያንዳንዱ መንደር ሳምንታዊ የወባ ሕሙማን ብዛት በሳምንትና በወራት ለአምስት አመታት በሚከተለው መንገድ ማዘጋጀት:: ለምሳሌ :-

ሠንጠረዥ 2 ለናሙና የቀረበ የወረርሺኝ መከታተያ ቻርት

| ዐመተ ምህረት | ሐምሌ | | | | ነሐሴ | | | | መስከረም | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1-7 | 8-15 | 16-22 | 23-30 | 1-7 | 8-15 | 16-22 | 23-30 | 1-7 | 8-15 | 16-22 | 23-30 |
| 1996 | 12 | 21 | 20 | 22 | 23 | | | | | | | |
| 1997 | 34 | 39 | 3 | 35 | 36 | | | | | | | |
| 1998 | 45 | 48 | 47 | 47 | 48 | | | | | | | |
| 1999 | 30 | 40 | 39 | 40 | 42 | | | | | | | |
| 2000 | 26 | 33 | 35 | 40 | 48 | | | | | | | |
| ከፍተኛ የሕሙማን ቁጥር | 45 | 48 | 47 | 47 | 48 | | | | | | | |
| ሁለተኛው ከፍተኛ የሕሙማን ቁጥር | 34 | 40 | 39 | 40 | 42 | | | | | | | |


2. ከአምስት አመቱ የሕሙማን ብዛት መረጃ በመነሳት በየሳምንቱ የታየውን ከፍተኛውንና ቀጥሎ ያለውን ከፍተኛ የሕሙማን ቁጥር መለየትና ማስቀመጥ:: ለምሳሌ ከሰንጠረዥ2 ላይ እንደተቀመጠው ከሐምሌ 1 እስከ 7 ያለው ከፍተኛ የሕሙማን ቁጥር 45 ሲሆን ቀጥሎ ያለው ከፍተኛ ቁጥር 34 ነው:: ከሐምሌ 8 እስከ 15 ያለው ከፍተኛ የሕሙማን ቁጥር 48 ሲሆን ቀጥሎ ያለው 40 ነው:: በዚህ ለሁሉም ሳምንታተ ይሰራል::

3. የወረርሽኝ መከታተያ ቻርት ላይ ሁለተኛውን ከፍተኛ የሕሙማን ቁጥር በመጠቀም የመስመር ግራፍ ለሁሉም ሳምንታት መሳል:: በዚህ መልክ የሚዘጋጀው የሁለተኛው ከፍተኛ የሕሙማን ቁጥር የመስመር ግራፍ ለየመንደሮቹ በየሳምንቱ የሚጠበቀው የወባ ሁኔታ ማሳያ ነው::

4. ለቀጣዩ አመታት /ለምሳሌ ከላይ ለተቀመጠው ሠንጠረዥ ለ 2001 ማለት ነው/ በየሳምንቱና

በየወሩ የሚሰበሰቡ የሕሙማን ሪፖርት ከተለመደው የሕሙማን ቁጥር ጋር ለማወዳደር መሰመር በቀይ ቀለም በመሳል የወረርሽኝ መከሰት አለመከሰቱን መከታተል ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 3 ለናሙና የቀረበ የወባ ወረርሺኝ መከታተያ ቻርት




5. በየሳምንቱ የሚሰበሰበው የወባ ሕሙማን ከተለመደው የሕሙማን ቁጥር / Normal chart/ ሲነካ ወይም ካቋረጠ ወረርሽኝ መከሰቱን ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም ወረርሽኝ መከሰቱን ለማረጋገጥ ወደ ሥፍራው መሄድ ያስፈልጋል፡፡

የግምገማ ሥራ ዓላማ

- ወረርሽኝ በትክክል መከሰቱን ለማረጋገጥ፣
- የወረርሽኝ መንስኤ ለይቶ ለማወቅ፣
- የበሽታውን የሥርጭት ስፋት ለማወቅ፣
- በጤና ላይ ያስከተለውን ጉዳት ለማወቅ ነው::

የወባ ወረርሽኝ ቁጥጥር እርምጃ የሚወሰነው በወረርሽኙ ባህሪና በአካባቢው በሚገኝ ግብአት ላይ የተመሰረተ ነው:: የቁጥጥር እርምጃዎችም

1. ትኩሳት ላላቸው ሕሙማን በሙሉ የፈውስ ሕክምና መስጠት፣
2. በሽታው የተከሰተባቸውን መንደሮች በፀረ ትንኝ ኬሚካል /በዲ.ዲ.ቲ/ መርጨት፣
3. ሕብረተሰቡ አጎበርን በትክክል እንዲጠቀም መቀስቀስና ትምህርት መስጠት፣

4. በተጨማሪም የአካባቢ ቁጥጥርና የፀረ ዕጭ ኬሚካል ርጭት ከላይ ከተጠቀሱት ጋር በቅንጅት ሊካሄድ ይችላል፡፡

የተከሰተው ወረርሽኝ ቀጣይነት እንዳለው የሚያሳዩ ባህርያት ማለትም የትንኝ መራቢያ ቦታዎች በብዛት መኖር፣ ነዋሪዎቹ የወባ ትንኝ በብዛት መኖራቸውን ካረጋገጡና የሕሙማን ቁጥር ከ30 በመቶ በላይ ሆኖ ከተገኘ የቤቶች ግድግዳ በፀረ - ትንኝ ኬሚካል እንዲረጭ ይደረጋል፡፡

## 8. የወባ በሽታ ለመከላልና ለመቆጣጠር የግልና የጋራ ጥረቶች

በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ

የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ራስንና ቤተሰብን ከትንኝ ንክሻ ለመከላከል ይቻላል፡፡ እነዚህም የትንኝ መከላከያ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በምሽት ጊዜ ሰውነትን ሙሉ በሙሉ ለትንኝ ንክሻ በማያመች መልኩ መሸፈን፣

- በሰውነት ላይ ትንኝ የሚያባርር ኬሚካል የያዘ ቅባት መቀባት
- በፀረ-ትንኝ ኬሚካል የተነከሩ አጐበሮችን መጠቀም፣
- የቤትን መስኮቶችና በሮች ጥቃቅን ቀዳዳ ባለው ሽቦ ወይም በአካባቢው ከተገኘ ቃጫ፣ ሰንበሌጥና አክርማ በተሠራ ወንፊት መሸፈን፣
- በተለምዶ ፊሊት ተብሎ የሚታወቁትን ፀረ-ትንኝ ኬሚካሎች በምሽት በቤቶች ውስጥ የአጠቃቀሙን መመሪ□ በመ□ቀም መንፋት፣
- የትንኞች እንቅስቃሴ ከምሽት እስከ ንጋት ስለሆነ ማንኛውም ቤት በነዚህ ጊዜያት ባይከፈት ይመረጣል፣

## የሕዝባዊ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድርሻ ፤

ከሕብረተሰቡ የሚጠበቅ

- የመኖርያ ቤቶችን ቦታ በጥንቃቄ በመምረጥ የወባ በሽታን ለመከላከል ይቻላል:: ይህም ማለት ትንኞች ሊበሩ የሚችሉት ከፍተኛ ርቀት 2 ኪ.ሜትር ስለሆነ ለሰዎች መኖርያነት የሚመረጡ ቦታዎች የወባ አስተላላፊ ትንኞች ሊራቡ ከሚችሉባቸው አካባቢዎች ቢያንስ ከሁለት ኪሎ ሜትር በላይ ርቀው መገንባት አለባቸው:: በተጨማሪም ብዙውን ጊዜ ንፋስ የሚነፍስበትን አቅጣጫ በማጥናት መኖርያ መንደር ንፋሱ ወደ ማይነፍስበት አቅጣጫ በማድረግ ትንኞች በንፋሱ ግፊት በቀላሉ እንዳይመጡ ለማድረግ ይቻላል::

- የወባ መከላከልና መቆጣጠር በተመለከተ በሚሰጠው ትምህርት ላይ በመሳተፍ የተማሩትንም በተግባር ላይ ማዋል፣
- ነዋሪዎች በየመንደራቸው በሚካሄደው የአካባቢ ቁጥጥር ሥራ ላይ በጉልበትና በማቴሪያል መሳተፍ፣

ከመንግሥታዊ ድርጅቶች የሚጠበቅ፡-

- የውሃ ማቆር ሥራ በሚካሄድበት ወቅት ለወባ ትንኞች መራቢያነት ምቹ ቦታ እንዳይፈጥር በየደረጃው የሚገኙ ባለሙያዎች የችግሩን አሳሳቢነት ተገንዝበው የውሃ መግቢያና መውጫያ ቦዮች ውሃ በማ□ቋዓሩበት መልክ መሥራት፣
- በመንገድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ከመንገድ ዳርና ዳር የሚቆፈሩ ቦዮችና አፈር ያወጡባቸው ጉድጓዳ ቦታዎች የዝናብ ውሃ ማቆር በማይችሉበት ደረጃ መደልደል፣

- የልማት ድርጅቶች ልማታቸውን ለወባ በሽታ ባልተጋለጠ መልኩ ማካሄድ አለባቸው::
- የመስተዳድር አካላት ህብረተሰቡን በማስተባበር መሳተፍ አለባቸው::

መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚጠበቅ:-

- ❖ በአካባቢው የሚገኙ አገር በቀልና አለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች በሚካሄደው የወባ መከላከልና መቆጣጠር ሥራ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ በስልጠና፣ ማቴሪያልና ገንዘብ እገዛ እንዲሳተፉ ይጠበቅባቸዋል::

## 9. ሰርቶ ማሳያ

በአራት ማዕዘን አጎበር አወጣጥር

- አጎበር ለመወጠር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች
- ሲባጎ
- ዘንግ (እንጨት ቁመቱ 2 ሜትር የሆነ)
- አጎበሩን በመኝታ ላይ መዘርጋት፣

- ዘንጉን ከአራቱ የአልጋ እግሮች ጋር ማሳር (ውጭ ከሆነ መሬት ላይ ዘንጎቹን መትከል)፣
- በአራቱ መአዘን ባሉ የአጎበር ቀለበቶች ላይ ሲባጎ በማሰር በተተከለው ዘንግ ላይ ወጥሮ ማሰር፣
- የአጎበሩን የታችኛው ዙርያ ጠርዝ ከፍራሽ ወይም ምንጣፍ ስር ማስገባት፣
- ከዚያም አጎበሩ ውስጥ ገብቶ መተኛት፡፡

*ማሳሰቢያ*

*አራቱ ማዕዘን ግድግዳ ላይ በተመቱ ምስማሮች ላይ መወጠር ይቻላል፡፡*

ባለ ክብ አጎበር አወጣጠር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

- በጣሪያ ላይ የተመታ ማንጠልጠያ
- ከአጎበሩ ጋር የሚገዛ ክብ ሽቦ
- ሽቦውን በአጎበሩ ቀጭኑ ክፍል በተዘጋጀው ማሡሪያዎች ዙሪያውን ማሡር፣
- መሃል ባለው ገመድ በመጠቀም አጎበሩን መስቀል፣
- በትክክል አልጋ /ምንጣፍ ስር ማስገባት

## 10. የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ኘሮግራሙ ከተጀመረበት ዓመት ጋር ሲነፃፀር፤

1. የሕብረተሰቡ ስለወባ በሽታ ምንነትና የመተላለፊያ መንገድ ግንዛቤና ክህሎት ያድጋል፣
2. በወባ ቁጥጥር ሥራ ላይ የሚሳተፍ ሕዝብ ብዛት ይጨምራል፣
3. የወባ ምልክትና ስሜት እንደተሰማው በ24 ሰዓት ውስጥ ሕክምና የሚያገኙ ሕሙማን ብዛት ይጨምራል፣
4. በወባ በሽታ የሚታመሙና የሚሞቱ ሰዎች ብዛት ይቀንሳል፣
5. የወባ ወረርሽኝ የተከሰተባቸው ጊዜያት፣ ወረርሽኙ ተከስቶ በዚሁ ወረርሽኝ የተጠቃ መንደርና ሕዝብ ብዛት ይቀንሳል፣
6. የወባ ትንኝ መከላከያ ዛንዚራ/አጎበር የሚጠቀም ሕዝብ ብዛት ይጨምራል፡፡

## 11. መልዕክት የማስተላለፊያ ዘዴዎች

በኅብረተሰቡ ተሳትፎ የወባ በሽታን ለመቆጣጠር ዋናዉ አንድ መሣሪያ የጤና አጠባበቅ ትምህርት በስፋትና በተለያየ ዘዴ ለሕብረተሰቡ መስጠት ነው፡፡

ብዙ የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች ቢኖሩም በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ደረጃ ሊተኮርባቸው የሚገቡ የተወሰኑ ናቸው፡፡

### ዋና ዋና መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች ፡-

1. አንድ ለአንድ መልዕክት የማስተላለፊያ ዘዴ
    - የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የቤት ጉብኝት በሚያደርጉበት ጊዜ ስለ ወባ ቁጥጥር አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ ከግለሰቦቹ ጋር መወያየት በሚሠራው ሥራ ከፍተኛና ግልጽ ተሳትፎ እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡

2. የቡድን ውይይት ማድረግ

- ከአንድ ሰፈር ለተውጣጡ በዕድሜና በፆታ ተመሳሳይ ለሆኑ ሰዎች አነስተኛ ሰው የያዘ ቡድን በመፍጠር ልምዳቸውን እንዲለዋወጡና እንዲማማሩ ማድረግ፣
- ከልምድ ልውውጥ በተጨማሪ ወባን ለመቆጣጠር ሰባራ እንስራ፣ ገል፣ ጠርሙስና የተጣሉ ጣሳዎች የዝናብ ውሃ ቋጥረው ትንኝ ሊያራቡ የሚችሉ ስለሆነ ማስወገድ እንዳለባቸው ማወያየት፣
- በምሽት የወባ ትንኝ ወደ ቤት ከመግባቷ በፊት በሮችንና መስኮቶችን እንዲዘጉና እንዲጋር□ ማስተማር፣
- በቤት ውስጥ የተለያዩ ጭስ በማጨስ ትንኝ ወደ ቤት እንዳትገባ መከላከል እንደሚቻል ማስተማር፣
- ሰውነትን በልብስ በመሸፈን ከወባ መከላከል እንደሚቻል ማስተማር፣

## 3. በትልቅ የሕዝብ ስብሰባ ላይ የሚሰጥ ትምህርት

- የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በትልቅ ሰብሰባ ላይ ለማስተማር የሚያቀርቡት ርዕስ ጉዳይ የአብዛኛውን ተሳታፊ ስሜት ሊነካ የሚችል መሆን ይኖርበታል፣
- በሕዝቡ ተሳትፎ ሊወገዱ የሚችሉ ውሃ ያቆሩ ቦታዎችን በተመለከተ ማወያየት፣
- በኬሚካል የተነከረ አጎበር መጠቀም ከወባ በሽታ እንደሚከላከል ማስተማር፣
- ማንኛውም ሰው ሲታመም በአፋጣኝ ወደ ሐኪም ቤት መውሰድ ጠቃሚ መሆኑን ማስተማር፣
- የሐይማኖት በዓላት ላይ ለተሰበሰበው ሕዝብ ትምህርት መስጠት፣
- በማንኛውም የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴ መልዕክት ማስተላለ□፣

## 12. ክትትልና ግምገማ

የክትትል ሥራ አንዴ ተሠርቶ የሚያበቃ ሥራ ሳይሆን ዕለት በዕለት ሥራዎች በታቀዱት መሠረት መካሄዳቸው የሚረጋገጥበት ዘዴ ሲሆን የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ዝርዝር ሥራዎች መከናወናቸውንና እነዚህን ሥራዎች ለማከናወን የተመደበ ግብአት ሥራ ላይ መዋሉን የሚረጋገጥበት መንገድ ነው፡፡

የክትትል አሠራር ቅደም ተከተል

- ዕቅዱን እንደገና መፈተሽ/ መመርመር፣
- ከእቅዱ አኳያ የተሠሩ ሥራዎችንና በአገልግሎት ላይ የዋለውን ግብአት ማነፃፀር፣
- የተሠራው ሥራና ሥራ ላይ የዋለው ግብአት ከወጣው ዕቅድ ጋር የተጣጣመ ከሆነ ሥራው በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን ስለሚያመለክት በዚያው እንዲቀጥል ማድረግ ነው፣

- ክንውን ዕቅድ በልጦ ከተገኘ ምክንያቱን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ግምገማ፡-

የተከናወኑት ተግባራት ከተያዙት ዝርዝር ዓላማዎች ጋር ምን ያህል እንደተጣጣሙ የሚታይበት ሥራ ነው፡፡ ግምገማ በግልና በቡድን የሚደረግ ሲሆን በግምገማ ጊዜ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች፡-

- የአለፉት ዓመታት ክንውኖችና የሚቀጥለው ዓመት ዕቅድ፣
- ዝርዝር ሪፖርቶች/ክንውኖች፣
- የአፈፃፀም ስልቶች
- ምርጥ ተሞክሮዎች ናቸው፣

የወባ በሽታ ቁጥጥር ግምገማ መለኪያዎች

1. በወባ ቀጥጥር ዙሪያ በግልም ሆነ በጋራ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት፣
2. የወባ ትንኝ መራቢያ ቦታዎችን ለማስወገድ በአካባቢ ቁጥጥር ላይ የተሳተፈ ሕዝብ ብዛት፣
3. የወባ ትንኝ መከላከያ ዛንዚራ (አጎበር) □ላቸው ሰዎች ብዛት፣

4. የወባ ትንኝ መከላከያ ዛንዚራ (አጎበር) ከገዙት ውስጥ እየተጠቀሙ ያሉ ሰዎች ብዛት፣
5. በወባ በሽታ የታከሙ የሕሙማን ብዛት፣
6. በዓመቱ ውስጥ በቀበሌው የተከሰተ የወባ ወረርሽኝ ብዛት፣
7. በወባ ወረርሽኝ ምክንያት ሕክምና ያገኙ ሕዝብ ብዛት፣
8. በወባ ወረርሽኝ የተጠቃ ቀጠና/ጎጥ ብዛት፣
9. ለከፍተኛ ሕክምና ወደ ጤና ድርጅት የተላኩ ሕሙማን ብዛት

*ዕዝል 1. የተከናወኑ ተግባራት ሪፖርት*

*ማድረጊያ ቅፅ*

**ኤክስቴንሽን ጣቢያው ስም ---------------------**

**ከተማ---------------------ወረዳ ----------------------**

**ወርና ዓ/ም---------------------**

**I. ሕክምና የተሰጣቸው (Morbidity)**

1. **በወሩ ውስጥ በወባ በሽታ የታከሙ ብዛት**
2. **ከታከሙት ውስጥ መድኃኒት የተሰጣቸው ብዛት**
3. **ወደ ከፍተኛ ጤና ድርጅት የተላኩ ብዛት**
4. **ከተላኩት ሕሙማን ውስጥ ሄደው ታክመው የዳኑ**
   - **በወባ ምክንያት ሆስፒታል ወይም ጤና ጣቢያ ተኝተው የታከሙ**
   - **ሆስፒታል ገብተው ወይም ጤና ጣብያ ተኝተው ከታከሙ የሞቱ**
   - **ሆስፒታል ወይም ጤና ጣቢያ ሳይደርሱ የሞቱ**

I. የአካባቢ ቁጥጥር

- በወሩ ውስጥ የተደረጉ ዘመቻዎች ብዛት
- በዘመቻ የተሳተፈ ሕዝብ ብዛት የተደፈኑና ቦይ በመቅደድ የተፋሰሱ፣ ውሃ ያቆሩ ቦታዎች በካ.ሜ
- የአቤት ኬሚካል የተረጨበት ውሃ በካ.ሜትር

II. የቬክተር ቁጥጥር

- የፀር ትንኝ ኬሚካል የተረጩ መንደሮች ብዛት
  ቤቶች ብዛት
- በተረጩ ቤቶች ውስጥ የሚኖር ሕዝብ ብዛት
- በወሩ ውስጥ አጎበር የገዙ ሰዎች ብዛት
- ጠቅላላ አጎበር የሚጠቀም አባወራ ብዛት
- አጎበር ያለበት ቤት ውስጥ የሚኖር ሰው ብዛት

## III. የወባ ወረርሽኝ ቁጥጥር

- የወባ ወረርሽኝ የተከሰተባቸው መንደሮች ብዛት፣
- የወባ ወረርሽኝ በተጠቃው መንደሮች ውስጥ የሚኖር ሕዝብ ብዛት፣
- በወባ በሽታ ተይዘው (የትኩሳት ስሜት ኖሮአቸው) የወባ መድኃኒት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት፣

ወረርሽኝን አስመልክቶ በሕዝብ የተሠሩ ሥራዎች ካሉ ይገለጹ

- የጤና ትምህርት የተሰጠበት ክፍለ ጊዜ (session) ብዛት
- በግልም ሆነ በጋራ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት

ሪፖርቱን ያዘጋጀው ስምና ፊርማ

ሪፖርቱ የተላከበት ቀን